# ዐማራው ከታዘለበት ከኢህአዴግ አንቀልባ ሊወርድ ይገባዋል!!!

## ከጎችዬ እንግዳ

ዐማራ ክቡር ሕዝብ ነው። ቅኝ ገዢዎች አፍሪካን የጨለማው አህጉር እያሉ ይጠሩ በነበረበት ዘመን፤ የዐማራው ህዝብ ሁላችንም የዐዳምና የሔዋን ልጆች በዓምላክ አምሳል የተፈጠርን ነን። በሰውና በሰው መካከል ልዩነት የለም። ይህንን የሚፈጽሙ ቅኝ ገዢዎችንም ቀይሀን አጋንንት ናቸው። ቅኝ ተገዢ ውንድሞቻችንንም ፀሊማን ወቅዱስ መናፈስት በማለት ይገልጿቸው ነበር። ዐማራው የእውቀት ምንጭ፤ የመውድስ፤ የድጓና የጾመ ደጓ ማዕክል ነው። ዐማራው ኢትዮጵያን ያሰፋ ያስተዋወቀና ያኮራ ህዝብ ለመሆኑ የታሪክ ድርሳናትን ማገላበጡ በቂ በመሆኑ መስካሪ አይሻም። በአጠቃላይ አገላለጽ የአፍሪካ እንቁ ፍርጥ ነው።

ዐማራ ዘረኛ አይደለም።በምስለ ክርስቶስ የተፈጠረ ሰበዐዊ ፍጡር ሁሉ የአዳም ዘር ነው ብሎ የሚያምን በመሆኑ ዘርና ቋንቋ ሳየገደበው ከሁሉም የኢትዮጵያ ለጆች ጋር ተጋብቶ፤ ተዋልዶና ደም ለደም ተቀላቅሎ ባህሉን ተውፌቱን ለሌላው በማጋራት በአጸፋውም የሌላውን ባህል አክብሮና የራሱ አደርጎ በመንከባከብ የኖረ ህዝብ ነው።

ኢጣሊያኖች ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛት ለማደረግ ያላሴሩት ሲራ ያልፈነቀሉት ድንጋይ የለም ማለት አይቻልም። በሰላይ ሚሲዮናቻቸው፤በዲፕሎማቲክ አወታራቸው ብዙ ሞክረዋል። ሙከራቸው ሁሉ ለምን ከንቱ ሆኖ እንደቀረ በመጨረሻ የተገነዘቡት ትልቁ ጉዳይ ቢኖር የዐማራው ህዝብ እስካለ ድረስ ህልማቸው እውን ሊሆን ያለመቻሉን ነው። በመሆኑም እንደ ስልት የቀየሱት የዐማራው ህዝብ በሌሎች ዘንድ  እንዲወገዝና እንደ ጠላት እንዲታይ ማደረግ ነበር።  አንዳንድ ነጭ ሚሲዮናውያንም ይህን ዘር ማጥፋት ነው፤ በሚል ሲገልጹ፤የአጠፋፉን አፈጻጸም በተመለከተ ከድንጋይ ጋር እያሰሩ ባህር መጨመር የሚል ዘግናኝ አስተያየት ሰጥተዋል።

ኢጣሊያኖች በመጀመሪያ ወደ ሀገራችን የገቡት በሰሜኑ የሃገራችን ክፍል በኩል ነው። ለዚህም ዋንኛው ምክንያት የሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በጂኦግራፊያዊ አቀማመጡ ከቀይ ባህር ጋር የተያያዘ በመሆኑ፡ይህንኑ ቀረቤታ በመጠቀም ነበር። የነዚህ ባእዳን ምድራችንን መርገጥ በብርቱ አጢነው ያዩት ሀቀኛ የኤርትራ ተውላጆችና እንዲሁም የትግራይ ልጆች፡ ምድራችንን ባእዳኖች አይረግጧትም፤ የመጡት ነጻነታችንን ለመግፈፍ፤ሀብታችንን ለመዝረፍና፤በመጨረሻም እኛን የእነሱ አገልጋይ ባሪያ ለማደረግ ነው። ስለዚህ ዝም ብለን ልናያቸው አይገባም። ወንድ ሴት ሳትል ተነሳ፤ስንቅህን ሰንቅ ጦርህንም ስበቅ ብለው በመነሳት    በተለያዩ ዐውደ ግንባሮች   በመዋጋት ከፍተኛ መስዋዕትነት ከፈለዋል። በአንጻሩም በሌሎችም ጎሳዎችና ነገዶች እንዳሉት የናት ጡት ነካሾች ሁሉ ከእንዚህም አካባቢዎች ለጠላት የተገዙ ሆድ አደር ባንዳዎች ነበሩ። በተለይ የትግራይ ሕዝብ በእነዚህ ሆድ አደር ባንዳዎች ላይ አንድ ወጥ ውሳኔ በማስተላለፍ ከማሕበራዊ ህይወት እንዲገለሉ፤በሚገጥማቸው ሀዘንም ሆነ ደስታ ማንም ሰው እንዳይቀላቀላቸው፤ ጋብቻም ቢጠይቁ ማንም ፈቃደኛ ሆኖ ልጁን እንዳይሰጥ፤ ይህንን ጥሶ የተገኘ ሁሉ ከነዚህ ጡት ነካሾች  ተነጥሎ እንዳይታይ ተማምሎ በመወስን ተግባራዊ አደረጎታል። እንደ ምሳሌም ማቅረብ የሚቻለው በሃገራችን ላይ የታሪካዊ ጠላቶቻችን የጥፋት መልእክተኛ የነበረው የእናት ጡት ነካሹ የመለስ (ለገሰ) ዜናዊ አባት የባንዳ ልጅ በመሆናቸው በትግራይ ምድር በሚስትነት የሚድረላቸው ተጋሩ በመጥፋቱ ወደ ኤርትራ ሄደው የሰርዐይ ተውላጆን አግብተዋል።

እንግዲህ የዐማራውን ህዝብ በጠላትነት ፈረጀው በሌሎችም ዘንድ እንደ ጠላት እንዲታይ ያደረጉት፣ በለስ የፈቀደላቸው፣የጌቶቻቸውን የኢጣሊያኖችን ውጥን ቀሪ ስራ አስፈጻሚና መልዕክተኛ በመሆን የበቀል ጥማታቸውን ለመውጣት የጣሩት እነዚሁ የባንድ ልጆች እነ መለስ (ለገሰ) ዜናዊ እና መሰሎቹ ናቸው።

ትህንግ ታላቁን የዐማራ ሕዝብ በታሪካዊ ጠላትነት በመፈረጅ በ1968 ዓ.ም. ባወጣው ማኒፌስቶ ዐማራው መጥፋት አለበት የሚለው አቋሙን ሲያራምድ ቆይቷል። ሥልጣኑን እንደያዘም ይፋ ተገባራዊ እንቅስቃሴ ጀመረ። ዐማራው በሰላም፣በአብሮነት ከሚኖርባት አገር ወያኔ ኢህአደግ እና ኦነግ ባደረጉበት ጸረ ህዝብ ቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳ፣ በሌሎች ወገኖቹ እንደ "ሰው በላ" እንዲታይ ሆነ። ይህ ደርዝ የለቀቀ የሀሰት ትርካ በሰላም የሚኖረው ህዝባችንን ላይ ያለ ሐጢያቱ ሃጠያተኛ፣ ያለ በደሉ በደለኛ ተደርጎ እንዲታይ በማስደረጋቸው፣ የህይወትና፣የአካልና ጉዳት፣ የንበረት ውድመት መፈናቀል አደረሶበታል። የያዘው የረዘዘው ሀብቱን ተዘርፏል። ትህነግም ሆነ ኦነግ የዚህ ዕኩይ ተግባር ሁነኛ ተዋንያኖች ሲሆኑ አርቆ አስተዋይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን እውነትና ነጋት እያደር ይገለጣል እንዲሉ ይህን ጸረ ዐማራ የቅስቀሳና የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ፣ከታሪክም ሆነ ከእውነት የራቀ፣የማሳሳቻና ተራ የፈጠራ ወሬ አርጎ በማየቱ አደጋው ተመጥኖል፣ ግን አልጠፋም።

ዐማራው ለ 28 ዓመታት ካብራኩ የወጡ ልጆቹ ባለመታመናቸው በላያቸው ላይ የሚሾሙ የወያኔ ኢ ህአዴግ እንደራሴዎች ሻቢያ እና ወያኔዎች ነበሩ። ማርም ሲበዛ የመራል ሆነና፣ ይህን ሁኔታ መቋቋም የሚቻለው እንደ ጠላቶቻችን ተደራጅተን ስንመክት ነው በማለት ፕሮፌሰር አሥራት የዐማራውን መደራጀት አበሰሩ። ዐማራው ለፍቶ ባቀናውና በገነባው አገር ተገፍቶ፣ተረግጦና የሰውነት ክብሩን ተንጥቆ መኖር አይችልም የሚለው የብዙሀን ዐማራ ድምጽ ተስተጋባ።

የጸረ አማራ ሀይሎች እየፈጠሩ ያለውን ችግርና ሰቆቃ መቋቋም የምንችለው አማራውን በማደራጀት በቻ እንደሆነ ታላቁ መሪያችን የጥሪ ደወላቸውን ደወሉ። ዐላማውንም በዝርዝር አስተማሩ። ድረጀቱንም መሰረት ለማሲያዝ ሲንቀሳቀሱ፣ ግዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ የሰብራል ሆነና እርሳቸውንና የቁርጥ ቀን የዐማራ ልጆች ወደ ዘብጥያ አወረዷቸው። ፕሮፌሰር አሥራትም የዚሁ የግፍ ጽዋ ተቋዳሽ በመሆን ክቡር ህይወታቸውን ለወገናቸው ቤዛ አድረገው አልፈዋል።

ግለሰቦችን ማሰርና መገደል ትግልን የማየገታ መሆኑን ዐዲሱ የዐማራ ድርጀት እያሳየ መጣ። የዐማራው መደራጀት ራስ መታት የሆነበት ትህነግ የማዕከላዊ መንግስቱን ሥልጣን ማደላደሉን በመተማመኑና ምንም ሊያመጡ አይችሉም በሚል፣ በትጥቅ ትግሉ ዘመን ኢህዴን ተብሎ የተደራጁ ርዝራዥ የኢህአፓ አባላት ነን ባዮች የመሰረቱትን የኢህአዴግ ግንባር አባል ድርጀት ከሕብረ ብሄራዊነት አውርደው ወደ ብሔር ድርጅትነት በመቀየር ብአዴን የሚል የዳቦ ስም ሰጡት። የዚህ ድርጅት አባላትና መሰራቾች ለህልውናቸው ያልቆሙ፣ ያለሙበትን የመጀመሪያ እቅድና ፕሮግራም የከዱ፣ ሌሎች በህልውናቸው ላይ እንዲያዙ የፈቀዱ፣ ሁኑ የተባሉትን የሚሆኑ፣ አድርጉ የተባሉትን የሚያደርጉ፣ ዛሬም ድረስ ከዚህ ሁሉ ሂደት የማይማሩ ናቸው።

ይህ ከህብረበሄራዊነት ወርዶ የአማራ ህዝብ ተውካይ ነኝ ያለው ብአዴን የትህነግ፣የኦነግና የሻቢያ እንዲሁም ጥቂት የደቡብ ተወላጆች ጥርቅምቅም ሲሆን፣ በቁኝጮነት የተሰየሙትም ከነዚህ ቡድኖች የተውጣጡ ናቸው። ለየስሙላ ያህል በተለያዩ መውቅራዊ ዘርፍ የሚያስቀምጧቸው ደግሞ በጉዳይ አስፈጻሚነታቸው የታመኑ ሆድ አደር ዐማራዎችን ነው። እንግዲህ ለዐማራው የመቶ ዓመት የቤት ሥራ ስጥተነዋል እያሉ የሚመጻደቁት በሴረኛነታቸው ከላይ ያሰቀመጧቸውን እንደራሴዎች በመተማመን ነው።

ብአዴን የዐማራው ሕዝብ መሪ ድርጀት ሆኖ ስልጣኑን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ፣በአደባባይ ሲታይ እራሱን ችሎ ህዝባችንን የሚያስተዳደር የሚመራ ይምሰል እንጂ በተግባር ግን ከበላዩ በተቀመጡ የጠላት እንደራሴዎቹ አማካይነት ምንም ዐይነት የዐማራውን የልማትም ሆነ ህዝባዊ ጥያቄ እንዳያስተናግድ ታፍኖ ያለ ድርጅት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል ። የወልቃይት ፣ጠገዴና ጠለምት እንዲሁም የራያና የመተከል የማንንነት ጥያቄና የመሬት ይዞታ ጉዳይ እስካሁን አልተመለሰም። ሀብት ንብረታቸውን ተገፈውና ተዘረፈው የተፈናቀሉ ወገኖቻችን እስካሁን ፍትህ አላገኙም። በግፍ የተገደሉወገኖቻችን ቤተሰቦች የደም ካሳ አልተከፈላቸውም። ይህንን አድራጊዎች አሁንም በሰላም ይኖራሉ። ብአዴን (አዴፓ) ለነዚህ ሁሉ ችግሮች ምንም ያደረገው ወይንም ለህዝብም ሆነ ለታሪክ ቀረጾ ያሰተላለፈው አንዳችም መረጃ የለም።

በለውጥ ሂደት ውስጥ ነን። ይህም ለውጥ በአማራውና በኦሮሞው ግንባር ቀደም መሪነት የመጣ ነው በሚባልበት ወቅት ለጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ አህመድ የወልቃየት የማንነት ጥያቄ ሲቀርብለት፣ የወልቃየት ህዝብ ጥያቄ መብራትና ውሀ ነው በሚል ያፌዘበት የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው። በራያ ያሁሉ ህዝብ ሲያልቅ እንደ ሰው ተቆጥሮ አልታየም። እንግዲህ በእንደዚህ ያለ ሁኔታ የሚገኘውን የአማራው መሪ ድርጅት ነኝ ባዩ አዴፓ ምንድነው የፈየደው? ይህ ሁሉ ሳየፈጸምና ሳይጠራ እንዴትስ መሪ ድርጅታችን ብለን እንከተለው?

በሰለላ ዐለም የተሰማሩ ግለሰቦች ዋንኛ ተግባራቸው ህዝብ ምን የላል የሚለውን ጥያቄ ማዋቅ ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ዐብይም ሆነ የመከላከያ ሚኒስትሩ ለማ መገርሳ ያደጉበት የሰራ ድርሻ ይህው ሰለላ እንደነበር በግልጽ ይታወቃል። በዚህ የሰለላ ቆይታቸው ስለ አትዮጵያ ህዝብ የተገነዘቡት ቢኖር ሃገር ወዳድነቱንና በኢትዮጵያ ከመጡበት ወደኋላ የማይል አይበገሬነቱን ነው። ይህም በመሆኑ በስለላ ስራቸው አጋጣሚነት የትግሬ ወያኔዎች አስተዳደር ህዝቡን ያስከፋው ኢትዮጵያዊነትን የሸረሸረ መሆኑን በጥልቀት ተገንዝብዋል። ምንም እንኳን እነዚህ ግለሰቦች የወጡት ወያኔ ከፈለፈለው ድርጅቶች አንዱ ከሆነው የ ኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ድርጀት (ኦህዴድ) ቢሆኑም ወያኔ የፈጠረውን ችግር መሰረት አድረገው፣ ስለ ኢትዮጵያና ስለኢትዮጵያዊነት በቃላት አጣፍጠው፣"አትዮጵያዊነት ሱስ ነው" "ስትፈጠርም ስትሞትም ስትቀበርም" ኢትዮጵያዊ ነህ የሚሉ ቃላቶችን በመሰንዘር አማለዉት ከዳር እስከዳር ደጋፍ ከመስጠቱም በላይ ፈጣሪ ኢትዮጵያን ለማዳን የላካቸው መልዕክተኞች ናቸው በማለት ሙሉ ድጋፍ በመስጠቱ የስልጣኑን ማማውን ለመንጠላጠል በቀቷል።

በዘር ፖለቲካ የተለከፈን ሰው ከፀበል መልሰው መላልሰው በያጠምቁትም ለግዜው የዳነ ይምሰል እንጂ ልክፍቱ እንደማይለቀው እሙን ነው። እነ ዐብይም የሰለላ ሙያቸው ለስልጣን አበቃቸው እንጂ ከያዛቸው የዘረኛነት ልክፍት አላላቀቃቸውም። ለዚህም ከብዙዎቹ መካከል እንድ ምሳሌ የማቀርበው 19 ባንክ በኦንግ ታጣቂዎች ሲዘረፍ አንዳችም ነገር ትንፍሽ አላሉም። በኦሮሞ ጉጂዎች የገዲኦ ህዝብ ሲሰቃይና ሲፈናቀል የሚመሩትን ህዝብ አመራር ባለመስጠታቸው ትልቅ ጉዳት ደረሷል። ይህም የሚያሳየው በስውር በጉዳዩ ያመኑበት፣የመስፋፋት ዐላማቸውን የሚያካትት በመሆኑ ጀሮ ዳባ ልበስ በማለት ነው። በሶማሊያ ክልል የተፈጠረውን በሚመለከት በውቅቱ የፌደራል መንግስት በመደረሱ ከብዙ ጉዳት ድኗል። ዐብይም ሆነ ደብረጽዮን ለማሰመሰል በአደባባይ በጎሪጥ ይተያዩ እንጂ በመካከላቸው ልዩነት የለም።

በቅርቡ በአማራው ክልል ለተፈጠረው አለመግባባት የሰው ህይውት ከመጥፋቱ በፊት ማዳን ይቻል ነበር ወይንስ አልነበረም።ይህንን ልሰውርም ቢሉት ለማይሰውሩት ለታሪክና ለህዝብ እንተዋለን። በሌላ በኩል ደግሞ፣መዋቅራዊ ዘርፉን በእያንዳንዷ የኢትዮጵያ መንደር በማሰፋት ማዕከላዊ የደህንነት ተቋም

የመሰረተ መንግስት መረጃ የለንም ማለት አይቻልም። ለችገሩ መፈትሄ አደርጎ የወሰደው ግን የፈደራል ልዩ ሃይል ወደክልሉ ማሰገባት ነው።

ይህ ሃይል ከገባ በኋላም ማጣራት በሚል ሰበብ ከፍተኛ የዐማራ ልጆች እንደቀድሞው ሁሉ ሰበዐዊ መብታቸው ተገፎ እየታሰሩ እና እንግልት እይደረሰባቸው ነው። የአብን ድርጅት አባላት ለዐማራው ህዝብ ባላቸው ወገንተኛነትና አለኝታ ተቀባየነት በማግኘታቸው፤የዐብይ መንግስት በክልሉ የተፈጠርውን ችግር አጋጣሚ አድርጎ በመጠቀም የበቀል እርምጃ እየወሰደ ይገኛል። የክልሉም አመራር በሁለት እግሩ ቆሞ የራሴን ጉዳይ እራሴ መፍትሄ እሻለሁ ብሎ መነሳት አለበት። ወደክልሉ የገባውን ልዩ ሀይል ባስቸኳይ ማስውጣት ይገባዋል። ይህን ሳያደርግ ቀርቶ ለሚከሰት ህዝባዊ ዐመጽ ተጠያቂ መሆኑ ግን አይቀርም። የሚበጀው እንደቀድሞው አድርግ የተባለውን ከማድረግ ተላቆ እንድ ጥንቶቹ አባቶቹ ጀግኖና የዜጎቹን መብት ማስከበር ይሆናል። በግፍ የታሰሩት ወገኖቻችን ብቻ ሳይሆኑ በነሱ መታሰር ለችግርና ለመከራ የተዳረጉት ቤተስቦቻቸውም ጭምር ከመሆኑም በላይ በመላው ዐማራ ህዝብ ላይ እይተካሄደ ያለ የሥነ ልቦና ሰለባ ነው። በመሆኑም በእስር ላይ ያሉ ወገኖቻችንን ባስቸኳይ መለቀቅ አለባቸው። ይህ ችግርና መከራ የማይሰማው ቢኖር በዐማራው ላይ በቀል ያዘለ ብቻ ነው ። አዴፓ አሁንም ከእንቅልፍህ ንቃ። ለሕዝቤም ቆሚያለሁ የምትል ከሆነ ዐማራው ከታዘለበት የኢህአዴግ አንቀልባ ውረድ። ከታሪክ ተጠያቂነት ለመዳን ፍቱን መድህኒቱ ይህና ይህ ብቻ ነው።

ከጎችዬ እንግዳ